OHCHR-EARO

# ኡቡንቱ




UNITED NATIONS HUMAN RIGHTS
OFFICE OF THE HIGH COMMISSIONER










ወይኔ ! ከእንግዲህ ትምህርት የለም?
ትዕግስት ትምህርት የሌለው ልንሞት ስለሆነ ነዉ ብላኛለች !
የመኝታ ሰአት . . .
እማዬ ! ሁላችንም ልንሞት ነው እንዴ?
በፍፁም ! በቫይረስ የሚመጣ በሽታ ብቻ ነው ! ስሙም ኮሮና ቫይረስ ነው።
ከእኛ የሚጠበቀው ዘወትር የምናደርገው የነበረውን በበለጠ ማድረግ ነው።
እጃችንን በደንብ መታጠብ፣
ፊታችንን በእጃችን አለመነካካት፣
ከሌሎች ሠዎች ጋር አለመነካካት፣
ወደ ውጪ በምንወጣበት ጊዜ አፍና አፍንጫችንን መሸፈን፣
ከጓደኞቻችን ጋር ለጊዜው አለመጫወት።
ባለፈው ትዕግስት የታመመች ጊዜ ይበልጥ የተጠነቀቅነው ትዝ ይልሻል? አሁንም ማድረግ ያለብን ይህንኑ ነው !
በነጋታው፣ ኤዮ ድንገት ከእንቅልፏ ስትነሳ አባቷ አያቷን በስልክ ሲያነጋግር ሰማች።
አያቴ አመማት እንዴ?


አትጨነቂ! አያትሽን አላመማትም፣ የደወልኩላት በየቀኑ ማውራት ስላለብን ነው።
ኮሮና ቫይረስ ትልልቅ ሠዎችን በይበልጥ ስለሚያጠቃ እጃችንን መታጠብ ያለብን ለዛ ነው፣ እራሳችንን መጠበቅ ያለብን ለዛ ነው፣
ለዛ ነው አያቶችሽ እኛ ቤት የማይመጡት፣ እኛም እነሱ ጋር የማንሄደው። ቫይረሱ ከኛ ወደ እነሱ እንዳይተላለፍ መጠንቀቅ ስላለብን ነው። ኮሮና ቫይረስ እንዴት ሊይዘን እንደምንችል ታስታውሻለሽ?
ካለመሃረብ ስናስነጥስ፣
እጆቻችንን ሳንታጠብ ፊታችንን ስንነካካ፣
ከጓደኞቻችን ጋር አብረን ስንውል፣
ከሌሎች ሠዎች ጋር ስንነካካ።
የአጎታቸው ልጆች ከአውሮፓ መጡ . . .
እማዬ! ከአጎታችን ልጆች ጋር መጫወት እንችላለን? ከእኛ ጋር እንደሚቆዩ አውቃለሁ ግን የሚኖሩት አውሮፓ ስለሆነ ቫይረሱ የያዛቸው ይመስለኛል።
ለምን?
ምክንያቱም ጎረቤታችን ወደ እዚህ የሚመጡትን ሠዎች ቫይረሱን እንዳያስተላልፉብን ሲባል ለረጅም ጊዜ ብቻቸውን መቆየት አለባቸው ሲሉ ሰምቻሉሁ።
አይ ኤዮ! እንደሱ እኮ አይደለም፤ ከሌላ ቦታ የሚመጡ ሰዎች ሁሉ ኮሮና ስላለባቸው አይደለም ተለይተው የሚቀመጡት በሽታው እንዳይሰራጭ ለማድረግ ነው። በይ አሁን ሂጂና ተጫወቺ!
ጎበዝ ኤዮ! እንደሱ ነው እጅሽን የምትታጠቢው!
እማዬና አባዬ፣ እንዳያመኝ የነገራችሁኝን ነገሮች ሁሉ እያደረግኩ ነው። አያችሁ፣ እጄን በደንብ እየታጠብኩ ነው። ይሄ ምንም አይከብድም! በፊትም እጃችንን ከመብላታችንና ከውጪ ስንመጣ እንታጠባለን። አሁን ደሞ ቶሎ ቶሎ መታጠብ ነው፣ ቀላል ነው!
ተፈፀመ